


# ፍየል፣ ዉሻና ላም

Fabian Wakholi
Marleen Visser
Mezemir Girma
Amharic
Level 2




ፍየል፣ ዉሻና ላም ጥሩ ጓደኞሞች ነበሩ። አንድ ቀን በታክሲ ጉዞ ለማድረግ ተነሱ።



ከጉዟቸው መጨረሻ ሲደርሱም ታክሲ ነጂው መሳፈሪያቸውን እንዲከፍሉ ጠየቃቸው። ላም የራሷን ሒሳብ ከፈለች።



ዉሻ ትንሽ ተጨማሪ ከፈለች፤ ምክንያቱም ትክክለኛው ዓይነት ገንዘብ ስላልነበራት ነው።



ሹፌሩ ለዉሻው መልስ ሊሰጣት ሲል ፍየል ምንም ሳትከፍል ሮጠች።



ሹፌሩ በጣም ስለተናደደ ለዉሻ ምንም መልስ ሳይሰጣት ሄደ።



ለዚያ ነው ዛሬ ድረስ ዉሻ መኪና በመጣ ቁጥር እየሮጠች መልሷን ያልሰጣትን ሹፌር ፍለጋ ወደ መኪናው ውስጥ ለማየት የምትሞክረው።



ፍየል የመኪና ድምጽ ስትሰማ ትሮጣለች። ምክንያቱም ሂሳብ ስላልከፈለች እንዳትታሰር ስለምትፈራ ነው።



ላም ግን መኪና ሲመጣ ምንም
አትጨናነቅም። መንገድም ስታቋርጥ ተረጋግታ
ነው፤ ምክንያቱም ሂሳብ የለባትማ።

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ፍየል፣ ዉሻና ላም


Written by: Fabian Wakholi
Illustrated by: Marleen Visser
Translated by: Mezemir Girma


This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 3.0 International License.